ፊታኙን ወቅት አልፈው በአዲሲ~ ኢትዮጵያ ምስረታ ላይ ወደር የሌለው ድርሻ ከተጫወቱት የኢህዴን ታጋዮች አንዱ የነበረው ኮበሌ በበለሳው እንቅስቃሴ ኢህዴንን በመመስረት ሂደት ላይ ድርሻውን በፅናት ተጫውቶ



ኢህዴን የዋግን ምድር ሰቆጣን ጨምሮ ለመጀመርያ ጊዜ ከደርግ አፈና ነፃ ሲያወጣ በኮማንደርነት እያዋጋና እየተዋጋ ቆይቶ

ሰቆጣን እንደገና ለመያዝ ከኮረም ከመጣው የደርግ ሰራዊት ወለህ ሃሙሲት በተባለ ቦታ ላይ የመከላከል ውግያ እያካሄደ እያለ ግራ ደረቱ ላይ በጥይት ተመታ

እናም ከኢህአ ጊዜ ጀምሮ አብራው የነበረችውም ማስታወሻውም አብራ በጥይት ተበርቅሳ ከልቡ አካባቢ ይፈስ በነበረ ደም ተነከረች

በቅርስነትም ከኢህኢዴን ብአዴን ታጋዮች ጋር እስከ 25ኛው የኢህዴን ብአዴን ምስረታ በአል ላይ ቆይታ ባህርዳር የሰማእታት ሃወልት ሲመረቅ አብራ ቆየችና በአእላፍ ህዝቦች ተጎበኘች

እናም አሁንም የኮበሌን ታሪክ አቁራ ከግኡዝነት አልፋ ይኸው ሽዎች ወጣቶችን ለፀረ ድህነት ትግል በኮበሌው መስመር አስተሳስራ ለታሪክ አሰልፋለች

# የኮበሌው ማስታወሻ

ስንቶች ተኮላሽተው ካረን০ ዘቀጡ
ስንቶች ተቸንፈው ከጎዳናው ወጡ
ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከክነው
ነግ እልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነው

ብሎ የዘመረ
ካልተንበረከኩት 37ቱ የኢህዴን ልጆች ጋር
በለሳ ተከዜ ፃኢ ተምቤን ምድር አብሮ የነበረ
ዋግ ሚስግ ሚካኤል ላይ

ርችት አምዘግዝጎ ድርብ ዕናት ቃሉን
የዘመን መሃላ የጠራ መስመሩን
በኩራት ያኖረ
ከጎንደር ከተማ በረሃ ላይ ወርዶ
በህዝብ ልብ ላይ ኮርቶ የሰፈረ
ኮበሌ የሚሉት አንድ ወጣት ነበረ

በገድል መቅድም ላይ በዋግ ምድር ንብራ
በኢህአዴግ ተጋድሎ በታሪክ አሻራ
ቃሉ እንዲፀና ተጠብቆ አደራ
ከዛ ከወደቀበት ስፍራ
ወለህ ሃሙሲት ወዲያ ወዲያ ወዲያ
ከመቃብሩ አፋፍ ወዲያ ወዲያ
መች በቃል ብቻ ተግባሩ ቃል ሆኖ አእላፍ እንዲጠራ
ያ ወጣት ኮበሌ
በዛች አፍላ እድሜ ላይ ወርቅ ታሪክ ሰራ

ነገ ሳይጠየቅ በትውልድ ወቀሳ
የህዝቦች አደራ ቃል ውርሱን ሳይረሳ
በፀና መስመር ላይ ቆሞ ለነብሱ ሳይሳሳ
ሞትን ገድሎ ሞተ ያ ኮበሌ አንበሳ
ዘላለም መኖሩን አውቆ አለፈ ገድሉ እየተነሳ

የኢህዴን የኢህአዴግ መስመር
ስፍሩ እንዳይጎድል ንብሩ እንዳይዛባ
ወለህ ላይ ሃሙሲት
ታዳሚ ሆነና ከጀግንነት አምባ
ታሪክ እማ« ሆኖ ያልተንበረከክነውን መዝሙር እያስተጋባ
ማስታወሻው ሳይቀር ደሙን እያነባ
በክብር ማለፉን ውሎው ይመሰክራል
ኮበል በተጋድሎው ቢሞትም ይኖራል

ኮበል ኮበሌው
ኮበሌው ኮበል
አንገቱን ሳይደፋ ኮርቶ እንዲያወድሰው
ያባቴ ስራ ነው እያለ እንዲጠቅሰው
በፈሩ እንዲቀጥል ብልህ ልጅ ተወልዶ
ትውልድ እንዲረከብ ተጋድሎ ተላምዶ
ማለፉ ዘላለም መኖሩ ነበረ ቁም ነገር ፈይዶ

ገድሉ ተንተርክኮ ትውልድ የሚያነቃ
በታሪክ ቅብብል ለውርስ የሚበቃ
ማስታወሻ ሆኖ እሚቆይ እንዳለ
ጥሩ ዜግነትን ውርስን የወከለ
ልጅ የሚከተለው አባትን ያከለ
በኢህአዴግ መስመር ቆርጦ የታገለ

ፈለግ ፈር ቀረቱ ማስታወሻ
ሆኖ ፈለግ ፈር ቀረቱ ይኸው
እልፍ ሆኖ ሃገርን ካኮራ
ኮበል የኢህዴን ልጅ
ኮበል የኢህአዴግ ልጅ
እሱም እንደማስታወሻው
ቢሞትም ይኖራል መልካም ስለሰራ

ኢያሱ በርሀ ግንቦት 19 2001
ከጀግናው ኮበሌ ለማስታወሻውና ለኢህአዴግ ወጣቶችና ሴቶች ሊግ ምስረታ